# ፖለቲካ በመረቅ

በላይነው አሻግሬ ምትኩ

አዳም ረታ “መረቅ” በሚለው ልቦለዱ ውስጥ የፖለቲካን አድማስ በጣም አስገራሚ በሆነ ድርጊት ያስነብበናል፡፡

አዳም ረታ “መረቅ” በሚለው ልቦለዱ ውስጥ የፖለቲካን አድማስ በጣም አስገራሚ በሆነ ድርጊት ያስነብበናል፡፡ እንደሚከተለው ነው፡፡

የአላዛር ፍቅረኛ ተባረኪ (ቴቢ) አንድ ቀን ቴአትር ስለምትሠራ ፍቅረኛዋን አላዛርን ቴአትሩን እንዲመለከት ትጋብዘዋለች፡፡ ለግላጋዉና መልከ መልካሙ አላዛር ደግሞ ጥሎበት በተለይ በዘመኑ ይሠሩ የነበሩ ቴአትሮችን አይወድም፤ ነገር ግን በእርሷ ግፊትና እርሷን ለማስደሰት ሲል ቴአትር ወደምትሠራበት ቦታ ሄደ፡፡

ከቴአትሩ በኋላ ግን አላዛር ቴአትሩንም ሆነ እርሷ የተላበሰችውን ገጸ-ባህርይ ፈጽሞ አልወደደውም፡፡ በቴአትሩ ውስጥ ያሉት ወዝ-አደር፣ ሠራተኛ፣ ፊውዳል፣ ምናምን የሚሉት ቃላት ፈጽሞ አልተመቸውም፡፡ ቴአትሩ ከተጠናቀቀ በኋላ ፍቅረኛው ቴቢ “እንዴት ነው ቴአትሩን ወደድከው?” ብላ አላዛርን ትጠይቀዋለች፡፡ ቀጥተኛው አላዛር ደግሞ ለምንም ሳይጨነቅ ምኑንም እንዳልወደደው ይነግራታል፡፡ የእርሷ (ወንዶች) ጓደኞችም እንዲሁ እየተመላለሱ ስለ ቴአትሩ ቢጠይቁት መልሱ አንድ ሆነ፤ በቃ አልወደድኩትም፤ ምኑም ደስ አይልም ይላቸዋል፡፡

ከዚያም ከፍቅረኛው ቴቢ ጋር ከቴአትሩ ግቢ ወጥተው ተያይዘው ወደ ሠፈራቸው ሊሄዱ ሲሉ አንድ ወጣት ቴቢን ለአንድ ጉዳይ እንፈልግሻለን ሲላት አላዛርን “ቆይ መጣሁ፣ ጠብቀኝ” ብላው ትሄዳለች፡፡ አላዛር ሆዬ አጥር ደገፍ ብሎ ፍቅረኛው ትመጣለች ብሎ ከርቀት እያያት ቆሟል፡፡

መጀመሪያ አንድ ሰው ጋር ቆማ ስታወራ ቆየች፤ ከዚያም ሌላ ተጨመረ፡፡ አላዛር ደግሞ አሁን ካሁን ትመጣለች እያለ ከርቀት እያያት፣ እርሷም በ‹እመጣለሁ ጠብቀኝ› እይታ ከርቀት ታየዋለች፡፡ ወሬ የያዛት ጎረምሳ ግን ወሬው በዋዛ የሚያልቅ አይደለም፤ በዚህም ምክንያት አላዛር ተሰላቸ፡፡ ይባስ ብሎም ብዙ ጎረምሶች ቴቢ ላይ እንደ ጎርፍ ሄደው ዙሪያዋን ከበው በወሬ ጠመዷት፡፡ አላዛር ከመሰላቸት አልፎ ብስጭት ገባው፤ እንዲያውም ሆን ብላ እርሱን ለማስቀናት ብላ እንዳደረገችው አሰበ፡፡

ነገር ግን ይህን ያቀነባበረው መጀመሪያ እርሱን ስለ ቴአትሩ ጠይቆት ነገር ግን እንዳልወደደው የነገረው ሰው ነበር፡፡ ምክንያቱ እንዲህ ነው፡፡ ቴቢ በወቅቱ ኅቡእ ድርጅት ውስጥ (ኢህአፓ) ገብታ ነበር፡፡ ቴቢ ደልዳላ፣ ቆንጆ፣ መልከ ቀና እና ሰው የምትስብ የ16 ዓመት አፍላ ኮረዳ ነበረች፡፡ በዚህ ውበቷ ምክንያት ሌሎች ጎረምሶችን እያማለለች ወደ ድርጅታቸው (ኢህአፓ) እንድታመጣላቸው ይፈልጋሉ፡፡ አላዛር ደግሞ ምንም ቆንጆ ቢሆን አስተሳሰቡ ከዘመኑ ወጣት የራቀ፣ ፖለቲካ ፈጽሞ ‹የማይገባው›፣ ግድ የሌለው ነበር (በዚያን ወቅት ኅቡእ ድርጅት መግባት፣ ትጥቅ፣ ትግል፣ ምናምን “ፋሽን” በነበረበት ወቅት አላዛር ግን ከዚህ “ፋሽን” የራቀ ስለነበር ነው፡፡) አላዛር ደግሞ የዚህ ነገር እንቅፋት እንዲሆን አይፈልጉም፡፡

ታዲያ ዋናው ቁም ነገር ምን መሰላችሁ? አላዛር ከርቀት እያየ ቴቢን ያ ሁሉ ጎረምሳ ሲከባት፣ ሲያዋሯት፣ አንዳንዴም እርሱን የጎሪጥ ሲያዩት በዚሁ ሰበብ ቴቢንና አላዛርን ማለያየት ዋና ዓላማቸው መሆኑ ነበር፡፡ ምክንያቱም ቴቢ ለኢህአፓ አስፈላጊ ስትሆን አላዛር ግን እርሷን በፍቅር ምክንያት ከትግሉ አስቀርቶ ድርጅቱ በእርሷ ቁንጅና ምክንያት ሊያገኝ የሚችለው ጥቅም ስለሚቀርበት ይህን አደጋ ከሩቅ ለማስቀረት ነበር፡፡ የሚገርመው ይህ ሒሳብ በደንብ የተሰላ ስለነበር ግቡን መትቷል፡፡ አላዛርም ሆነ ተባረኪ ሒሳቡን ሳያውቁት ሁለቱም ተበልተዋል፤ በፖለቲካ ሽክርክሩ ተረትተዋል፡፡ ምክንያቱም ያቺ ዕለት በሁለቱ ፍቅረኞች፣ በአላዛርና በቴቢ፣ መካከል የመጀመሪያዋ የመራራቃቸው ጥንስስ ሆነች፤ ያች ቅጽበት ለሁለቱ ፍቅር አንድ መለያያ ነጥብ ሆነች፡፡ (ከዚያ በኋላ በደም ቢተሳሰሩም እንኳ ወደ ቀድሞ ፍቅራቸው ሲመለሱ አናነብም፤ አልተመለሱምም፡ ፡)

አዳም ረታ ከዚህ ላይ ነው ዋና መልእክቱን የሚነግረን፡፡ አላዛርንና ቴቢን የማለያየቱ ሥራ የተጠና የፖለቲካ ሥራ ነው፡፡ ግቡንም በአግባቡ መትቷል፡፡ በትልልቅ አገራዊ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ስንት ክርክር፣ ውሳኔ፣ ትግል፣ መጠላለፍ፣ ደባ፣ ሸር፣ ... ሌላም ሌላም ያለበት ፖለቲካ ወደ ታች ወደ ሰፈር፣ ወደ ጓደኞች፣ ወደ ፍቅረኞች ሲወርድ በእንዲህ ያለ ርካሽ መልኩ ነው፡፡ ፖለቲካ ማለት በትንሹ ይህን ይመስላል፡፡

(የራሴ) በተመሳሳይ መልኩ በትልልቅ ደረጃ የምንሰማቸውና የምናያቸው ሙስና፣ ዘረኝነት፣ ትልልቅ የሙብት ጥሰቶችና ሕገ-ወጥነቶች፣ ... ሌላም ሌላም የምንለው ወደ ታች ሲወርድ በነአላዛርና ቴቢ እንደደረሰው ሁሉ ርካሽ በሆነ መልኩ ነው፡፡ እነዚህ ትልልቅ ድርጊቶች ከታች ከግለሰብ ጀምረው የሚሠሩ ጥቃቅን ሙስናዎች፣ የሙብት ጥሰቶች፣ ሕገ-ወጥነቶች ተሰናስለውና አድገው የሚያስከትሉት ድምር ውጤቶች ናቸው፡፡ ለዚህም ነው ከላይ ያሉ በትልልቅ ደረጃዎች ያሉ ጥፋቶች የሚወገዱት ከሥር ጀምረን እያስተካከልን ስንመጣ ነው የሚል የጸና እምነት ያለኝ፡፡

---